# ተሰማ ካስመራ ወሬ!

ተሰማ ካስመራ ወሬ፣
ተሰማ ካስመራ ወሬ፣
እሆሆ፣ እንዴና ብሬ...

መሸገው ኢሳያስ ጎሬ
"ታጠቁ የትግል ሱሬ"
እሆሆ፣ እንዴና ብሬ...

"ያፈቀርዋትን ኢትዮጲያ"፣
ሊያነድዋት በእሳት ቿያ፤
እሆሆ፣ እንዴና ብሬ...

እንደሸማኔ መወርወሪያ፣
ባከኑ ወዲህና ወዲያ፣
እሆሆ፣ እንዴና ብሬ...

ያነዜም ሳለ ኢህአባ
ፈርጥጦ ካርቱም ሳይገባ
እሆሆ፣ እንዴና ብሬ...

"ይገባ ነበር ከሳቱ
ብርሽ ቆፍጣና አሞቱ፤"
እሆሆ፣ እንዴና ብሬ...

ዜግነት ተንግሊዝ ጉያ፣
ሸጉጦ እንዴ ማፈርያ፣
እሆሆ እንዴና ብሬ!

ይመክራል ከኤርትርያ፣
"ሊሞትላት ለኢትዮጲያ"፤
እሆሆ፣ እንዴና ብሬ፤

ባስመራ ተሰማ ወሬ፣
ብርሀኑ ታጠቀ ሱሬ፤
እሆሆ፣ጉድ በይ አገሬ!

ባስመራ ተሰማ ወሬ፣
አንዳርጌ ታጠቀ ሱሬ፣
እሆሆ ጉድ በይ አገሬ!!
እሆሆ ጉድ በይ ሀገሬ!!!

**Mezmur Fukare 05/29/09**